# የሴክተሩ መዋቅር

- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ጤና ቢሮ
  - ዋና ቢሮ ሃላፊ
    - የ ኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ቢሮ ሃላፊ
      - የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር II
      - የህዝብ ግንኙነትና የኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት I
      - የፋይናንስና የክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬት II
      - የክፍያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር II
      - የግዥ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር II
      - የእቅድ ዝግጅትና ክትትል ግምገማ ዳይሬክቶሬት
    - የስርዓተ ጾታ ጉዳይ ቡድን መሪ
    - የህግ ባለሙያ IV
    - የሰነ ምግባር መኮንን
    - የፕሮግራም ዘርፍ ምክትል ቢሮ ሃላፊ
      - የእናቶች ወጣቶች እና ህፃናት ጤና ክብካቤ ዳይሬክቶሬት
      - የኤች አይ ቪ ኤድስ ዘርፈ ብዙ ምላሽ ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት
      - የምግብ ጤናና ጤና ነክ ተቋማት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት
      - የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምና መሰረታዊ ጤና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
      - የክሊኒካል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
      - የጤና መድህን የጤና አገልግሎት ክፍያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

## የሴክተሩ ምስረታ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ካሉ አስራ ሁለት ክልሎችና ሁለት የከተማ አስተዳደር አካባቢዎች በስተሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኝ ክልል ነው። ክልሉ በ1987 ዓ.ም (1995 G.C.) የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ከፀደቀ በኋላ እንደ አንድ ክልል መቋቋሙን ተከትሎ፣ የጤና ቢሮው የተቋቋመው የፌዴራል ጤና ሚኒስቴር የሥራ ድርሻዎችንና ኃላፊነቶችን በክልል ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ነው:: በዚህ መሰረት ቢሮው የክልሉን ህዝብ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት ለማረጋጋጥ በተወሰኑ ጤና ተቋማት ለህብረተሰቡ አገልገሎት መስጠት የጀመረ ሲሆን ከዛም አገልግሎቱን በዞን፣ በከተማ አስተዳደር፣ በወረዳ እና እስከ ቀበሌ ድረስ የጤና ስርአት በመዘርጋት እና የሰው ሃይል በሟሟላት ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ሥልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 197/2015 ዓ.ም ዳግም የተደራጀ ሲሆን አጠቃላይ ስራዎችን ለመስራት እንደ ሀገር አገልግሎት ላይ ያለውን የጤና አገልግሎት እና ቁጥጥር አዋጅ 1362/2024ን ይገለገላል።

## የሴክተሩ ደንቦችና መመሪያዎች

ቢሮው ከሚጠቅምባቸው አሰራሮች እና የአስተዳደር ስራዎችን የሚያቀላጥፍባቸው መመሪያዎች እና ደንቦች መካከል:-

i. የኤድስ ፈንድ አጠቃቀም መመሪያ:-2003ዓ/ም
ii. የኤች/አይ/ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ መመሪያ (የ2% በጀት አጠቃቀም መመሪያ) 2012ዓ/ም
iii. የጤና ግብዓቶች ለመቀያየር እና አዘዋውሮ ለመጠቀም የወጣ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 04/2016
iv. የጤና ጣቢያ የጤና ሃብት ማግኛ ሪፎርም ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 05/2014
v. ስነ ምግብ መደሃኒት አስተዳደር ደንብ ቁጥር 168/2016
vi. የጤና አገ/ት አስተዳደር እና ቁጥጥር ደንብ ሰኔ 2017
vii. የጤና ባለሙያዎች እና የምግብ ተቋሚት ምዝገባና የሙያ ስራ ፍቃድ አሰጣጥ ክፍያ የኢኒስፔክሽን መመሪያ
viii. የቤ/ጉ/ክ/መ የባህልዊ ህክምና አስተዳዳር ቁጥጥር መመሪያ 2008
ix. የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ 150/2010

የበሽታ መከላከልና መቆጣጠር ዳይሬክቶሬት

x. የጤና ባለሙያዎች ቅጥር የወጣ መመሪያ 3/2013

xi. የተሸሻለ የዲሲፕሊን አፈፃፀም እና ቅሬታ ይግባኝ አቀራረብ ደንብ ቁጥር 138/2011

xii. የትምህርት እና ስልጠና መመሪያ ቁጥር 02/2011

xiii. የቤ/ገ/ክ/መ/የሰ/ሀ ስራ አመራር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 01/2011

xiv. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ የፋይናንስ አስተዳደር ቁጥር 95/2003

xv. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ የግዥ አፈፃፀም ቁጥር 13/2003

## የስክተሩ የሰው ሃይል

በጤናው ዘርፍ እስከ አሁን የተሰማሩ ቋሚ የጤና ባለሙያዎች እና አስተዳደር ሰራተኞች በጠቅላላ 7351 ሲሆኑ ከዚሁ መካከል 49.8% ወንድ ሲሆን ቀሪዎከቹ 50.2% ሴቶች ናቸው ከዚህም መካከል 4797 የሚሆኑት የጤና ባለሙያዎች ሲሆኑ 2554 የሚሆኑት የአስተዳደር ሰራተኞች ሲኖሩ በክልሉ መንግስት በጀት የተቀጠሩ 45 የኮንትራት ሰራተኞች አሉ፡፡ የክልሉ የጤና ባለሙያ ለህብ ጥምርታ በ2008 ከነበረበት 2.7 ለ1000 በአሁኑ ሰዓት 3.77 ለ1000 ህዝብ ነው